# ምርጫ ሲደርስ የሚወለዱ ፓርቲዎች !

**ታደገ ከካዛንችስ** (tadmeng@yahoo.com )

የፊውዳል ሥርዓት አገዛዝን በመቃወም በተማሪዎች በተቀጣጠለ አብዮትና በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተከፈለ መስዋዕትነት ደርግ ወደ ስልጣን ሊመጣ እንደቻለ ታሪክ ይዘክራል፡፡

ደርግ በትረ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ የስልጣን ተቀናቃኞቼ ያላቸውን በጅምላ ጨፈጨፋቸው @ የተቀሩትንም በእስር እንዲማቅቁና ከአገር እንዲሰደዱ አደረገ።በዚህን ጊዜ የደርግን የግፍ አገዛዝ በመቃዎም ብሶት የወለዳቸው የህዘብ ልጆች አንባገነኑን የደርግ መንግስት በትጥቅ ትግል ለመፋለም በርሃ ወረዱ።

በአፄዎቹም ሆነ በደርግ ስርዓት ህዝቡ በነፍጠኞች ፍላጐትና ጫና ስር ወድቆ በእነርሱ መልካም ፈቃድ ነበር የሚኖረው። በስርዓቶች ይህን መቃወም ለስቃይና ለሞት ከመዳረግ በቀር የሚፈይደው አንዳች ነገር አልነበረም፡፡ ህዝቡም ይህ ይስተካከል የሚል አቋሙን ለመግለፅ ከሞከረም እጣፈንታው ሞት፣ እስርና፣ ስደት ብቻ ነበረ፡፡

ታድያ በእነዚህ ኋላቀር ስርዓቶች ህዝቡ በመረጠው የመተዳደር መብት የለውም፣ አምባገነኖች ስልጣንን በሞኖፖል ተቆጣጥረው ህዝቡን በግፍ እያስተዳደሩት ኖረዋል። የሚቃወማቸውንም እንደጠላት በመቁጠር በግፍ ይቀጡ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያዊያን ዘር፣ ሀይማኖትና ፆታ ሳይለያቸው ነፃነታቸውን ለማረጋገጥ ትውልድ ሊያኮራ የሚችል የአብሮነት ታሪክ ሠርተው አልፈዋል፡፡ይህ ታሪክ ግን የበርካቶችን የህይወትና የአካል

መስዋዕትነት የጠየቀ ነበር። ዛሬ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በመረጡት የመተዳደር ፣ በቋንቋቸው የመማርና የመዳኘት ፣ ባህላቸውን የማሳደግ መብታቸው ተከብሮላቸዋል።

የወታደራዊው ደርግ ኢሰፓ መንግስት ሲወድቅና የኢትየጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ የስልጣን መንበሩን ሲጨብጥ ለሽግግር መንግስት ምስረታ የተለያዩ አቋም ያላቸውን ፓርቲዎች እንዲሳተፉ አደረገ፡፡ ገና ከጅምሩ ኢህአዴግ ህዝባዊ ፓርቲ መሆኑን ያስመሰከረው በሽግግር መንግስት ምስረታ ሁሉንም ተቃዋሚዎች መጋበዝ መቻሉ አንድ ማሳያ ነበር።

የአገራችን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ታሪክ እጅግ አስገራሚ ነው።የተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚመሰረቱት የህዝብንና የአገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ሳይሆን የግለሰቦችን ጥቅማ ጥቅም ለማስከበር ነው።በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ ፓርቲዎች ህዝባዊ መሰረት የላቸውም።

በኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የመደራጀትና አፍታም ሳይቆዩ የመበታተን አባዜ እስከ አሁን የዘለቀ ነው። በ1997ዓ/ም ምርጫ ወቅት የተፈጠሩት የፓርቲዎች ጥምረት ለህዝቡ መነቃቃትንና አዲስ የፖለቲካ መንፈስን የፈጠረ ነበረ፡፡ ይሁን እንጂ የተፈጠረው ጥምረት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ የወራት ዕድሜ እንኳን ሳያስቆጥሩ መበታተን እጣ ፈንታቸው ሆነ።

በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው የተባለውን አዲስ የፖለቲካ ባህል ይዘው ወደ ምርጫ የመጡት «ቅንጅት»በሚል ስያሜ ወደ ምርጫ ቢገቡም ከምርጫ በኋላ ብዙ ርቀት መራመድ አልቻሉም፡፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ዘላቂ ጥቅም ሰንቀው ለትግል ባለመነሳታቸው መሰነጣጠቅና መፈረካከስ አይቀሬ ሆነ ፡፡

ለህዝብና ለአገር ጥቅም ሲሉ የተቀናጁ ባለመሆናቸው ህዝብ በድምፁ የሰጣቸውን የምክር ቤት መቀመጫ የህዝብ ውክልና መሆኑን ተገንዝበው የጠራ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርፅው ወደ ተግባር መግባት በቻሉ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ተቃዋሚዎች መጀመሪያውኑ ቅንጅትን ሲመሰርቱ እርስ በእርስ የሚጋጭ ፍላጎት ስለነበራቸው ሊጣጣሙ አልቻሉም፡፡

በ1997ዓ/ም በተደረገው ምርጫ የተገኘውን ውጤት በፀጋ ተቀብሎ ወደተግባር ከመግባት ይልቅ በአላሸነፉበት ቦታም መንግስትን ይልቀቅልን በማለት በፈጠሩት ሁከትና አመጽ የበርካታ ንጹሃን ዜጎች ህይወት አልፏል፡፡ ንብረት ወድሟል፡፡ በርካቶች ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል፡፡ ይህም የራሱ የሆነ የብስለት ችግር ነበረው፡፡ ከዚህ ጐን ለጐንም ፓርቲዎች በውስጥ ችግር በመታመሳቸው እንኳን ህዝብን ሊመሩ እርስ በእርሳቸው እንኳ መደማመጥ አልቻሉም።

በአደባባይ እርስ በእርሳቸው ሲባሉ& ለልጣን ሲሻኮቱ & ሰባዊነት በጎደለው መልኩ ሲዘላለፉ ታይተዋል።ውድድር ካለ ማሸነፍና መሸነፍ ያለና የሚኖር ነው። የኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተወዳደሩበትን የምርጫ ጣቢያ ብቻ ሳይሆን ያልተወዳደሩበትንም ጭምር አሸንፈናል በማለት ህዝብን ለሁከትና ብጥብጥ አነሳሱት& ስልጣንን በአቋራጭ ለማግኘት ካላቸው ህልም የተነሳ አገርንና ህዝብን በሚጎዳ የስርዓት አልበኝነት ተግባር ላይ በይፋ ተሰማሩ።

ይህን አመፅ የማቀጣጠልና የመምራት ድርጊት ወንጀል በመሆኑ በቁጥጥር ስር ውለው በነፃው ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸው በይፋ የፍርድ ሂደት ጥፋተኝነታቸው ተረጋግጦ ቅጣት ተዎስኖባቸዋል።

ነገር ግን ከዚህ በኋላ የቅንጅት አመራሮች ከስህተታችን ታርመናል &የኢትየጵያን ህዝብ በድለናል በማለት ለመንግሥትና ለህዝብ ባቀረቡት

የይቅርታ ጥያቄ መሠረት በቅድመ ሁኔታ ላይ በተመሠረተ ይቅርታ ተደርጎላቸው ከእስር ተፈቱ ።የተወሰኑት በይፋ ይቅርታውን በአደባባይ አንፈልግም አንጠይቅም በማለታቸው ወደ ማረሚያ ቤት ተመልሰዋል።ሌሎች ደግሞ የገቡትን ቃል አጥፈው ወደ ቀድሞው አፍራሽ ድርጊታቸው ተመልሰዋል። ይህ ብዙዎችን አስገርሟል።

የባለፈውን በዚህ አብቅተን በአሁኑ ጊዜ እርስ በእርስ ስለሚናከሱ ፓርቲዎች ምንነት በመጠኑ እንመልከት፣ ከቅንጅት መፍረስ በኋላ የቅንጅት ወራሽ ነኝ ብሎ የተመሰረተው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በተመሳሳይ የመበታተን አደጋ ተጋርጦበታል፡፡ የአደጋው መንስኤ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

ስለመበታተናቸው ሁሌም የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች « ግልፅነት የለም የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አይከበርም፣ የጥቂት ግለሰቦች አምባገነናዊነት ነግሷል ወዘተ...» የሚሉ ተመሣሣይነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም ቢሆን «እገሌ የሚባለው ቡድን ነው እንዲህ ያደረገው፣ እኔ አይደለሁም» በሚል ከመወነጃጀል ባለፈ «የችግሩ ምንጭ ይሄ ነው ወይም እኔ በዚህ መልኩ ስህተት ሠርቻለሁና በዚህ መልኩ ይስተካከል» ብሎ ያመነም ይሁን ለችግሩ መንስኤ ራሱን ተወቃሽ የሚያደርግ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ ማየት አልቻልንም።

እነርሱ እራሳቸው የሚያወጡትን የፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ ፣የዴሞክራሲ መርህና ሌሎች ለዲስፕሊን ተገዢ የሚያደርጉ ህጎችን እነርሱ እራሳቸው ያላከበሯቸውን ማን እንዲያከብርላቸው ይሆን የሚፈልጉት? ልብ ያለው ልብ ይበል!

ሌላው የሚሰተዋል ሃቅ ደግሞ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ቀደም ባሉት ጊዜያት በራሳቸው የውስጥ ችግር ምክንያት ተጠላልፈው ከወሬ ባለፈ አንዳችም ቁም ነገር መስራት ቸግሯቸው ሲፈረካከሱ ታይተዋል።

ለዚህ ችገራቸው ደግሞ ዋና ተጠያቂ ኢህአዴግን የማድረግ አባዜ የተጠናወታቸው መሆኑን ነው፡፡ #የእናቴ መቀነት---; እንደሚባለው።

እውነቱን ለመናገር ግን ለመበታተናቸው ዋናው ምክንያት ገዥው ፓርቲ ሳይሆን የራሳቸው የውስጥ ችግር መሆኑን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚደራጁት አገርንና ህዝብን ከመጥቀም አንፃር ሳይሆን የተወሰኑ ግለሰቦችን ጥቅምና ዝናን ለማስጠበቅ ታስቦ ነው። በዚህም ምክንያት የተነሱለትን ዓላማ በመርሳት ከድርጅታቸው ጉዳይ ይልቅ የግል ጥቅማቸውን ማስቀደማቸው &ርካሽ ተወዳጅነትንና ታዋቂነትን ለማግኘት የሚያደርጉት መሯሯጥ የቆሙለትን አላማ እንዲረሱት ያደርጋቸዋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታም መረዳት የሚቻለውም ይህንን ነው፡፡ የፓርቲው ህገ ደንብ አልተከበረም &የፓርቲው ገንዘብ ከስርዓት ውጪ ባክኗል ፣ እነዚህ አባላት ከፓርቲው መታገድ አለባቸው ወዘተ በማለት ንትርካቸውን ቀጥለዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የራሳቸው የአመለካከት ችግር እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

መቼ ይሆን የግለሰቦች ችግር የፖለቲካ ጉዳይ ከመሆን ወጥቶ ወደ ዋናው አንገብጋቢ የአገር ጉዳዮች የሚዞረው? የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ከአሉባልታና ከእንካ ሰላንቲያ ተላቀው በአማራጭ ፖሊስና ስትራቴጂዎች ላይ የሚያተኩሩት? እውነቱን ለመናገር በአሁኑ ጊዜ እኮ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ምን አይነት አቋም እንደያዙ ለህዝቡ ግልፅ አይደለም፡፡ ዛሬ አንድ ነገር ሹክ ይሉናል ፣ውሎ ሳያድር ሌላ ይተርኩልናል #ላም አለኝ በሰማይ---;።እባካችው ግራ ገብቷችው ግራ አታጋቡን።

ግለኝነትን ማዕከል ካደረገ አስተሳሰብ ተላቆና ለጋራ ጥቅም ራስን አስገዝቶ የሚታገል ተቃዋሚ የሚፈጠርበት ጊዜ ናፍቆናል። እስከ አሁን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የፖለቲካ ባህል መሠረታዊ ልዩነቶች እያሉባቸውና በአይዲዮሎጅም የማይገናኙ ፓርቲዎች በአንድ ጥላ ስር መሰባሰብና ትንሽ ሳይቆዩ መበታተን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለአገርም ለህዝብም የሚበጅ ስራ እንዳይሰሩ ያደረጋቸዋል።

በመሆኑም የአገራችን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተነጋግሮ ከመተማመን ይልቅ ልዩነትንና መጠፋፋትን፣ ከድርጅት ጥቅም ይልቅ የግል ጥቅምንና ዝናን ማግበስበስን መምረጣቸው ለመበታተናቸው ዋናው ምክንያት ነው ብል አልተሣሣትኩም፡፡

ይህም ሊሆን የቻለው አስበውበትና ጠንካራ መርህ ይዘው መነሳት ባለመቻላቸውና በአብዛኛው ፓርቲዎች የሚወለዱት ምርጫ ሲደርስ በመሆኑ ችግሩን የከፋ ሊያደርገው እንደቻለ መረዳት ይቻላል፡፡ ለችግር መፍትሔ ይሆን ዘንድም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቀደም ብለው ቢወለዱ ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡